# ትግሉ ባስቾኳይ ይቀየር

ደራሲ - አሚን ዞሮመጣ

የሰው ልጅ ጠላቱን ማወቅ ከተሳነው
ተማረ አልተማረ ሁሉም ፋይዳ የለው
እያየ እየሰማ ሚስጥሩ ካልገባው
አሽከርና ጌታ መለየት ካቃተው
ወሳኝ ትግል ማድረግ እንዴት ነው ሚቻለው?

መለስ መሪ አይደለ እንደራሲ ነው
እምዬን ለማጥፋት መድሀኒት ነው ብሎ ፈረንጅ የሰራው

ቂሙን የማይረሳው ፈረንጅ መሰሪው
እኛን ሳያማክር በአገራችን ላይ ወያኒን ሾመው
ከዚያም እንዲህ የሚል መመሪያ ሰጠው
በዘር በሀይማኖት ከፋፍለህ ግዛው
ያለ ርሕራሂም ከፍ ዝቅ አድርገህ ሕዝቡን አዋርደው
ታሪኩን በሙሉ እንዳልነበረ አርገህ በደንብ በክለው
ይህንን ካደረክ - የኛ ድጋፍ ላንተ አስከዘላለሙ የሚቀጥል ነው

እሱም አልቦዘነ ለብዙ አመታት
አገሪን ክፉኛ በሽብር መታት
ሕዝቡም ተጋለጠ ለማይሆን ስደት
አገር ቢት ያለውም ሱባኢ ቢገባ ጠሎትም ቢያደርግ
ምንም አልጠቀመው ታረደ እንደ በግ

CIA በክንፉ Mossad በክናፉ እየጠበቀው
እርዳታ አስመስሎ ያማሪካን ዶላር ጉቦ ሲያሸገው
ያልተመረመረ ያልታወቀ ምግብ ሕዝቡን ሲያበላው
መቃወም ሲገባን ዝም ብለን አለፍነው
ይዘገያል እንጂ የኋላ የኋላ የሚያስጠይቀን ነው

እረ ለመሆኑ አማካሪ አድርጎ ማነው የሾመው
ባገራችን ጉዳይ ማንም ሳይጠይቀው እጁን ያስገባው
ተው አርፈህ ተቀመጥ ብለን ካላልነው
እንዲሁ ቁጭ ብለን ማለቃችን ነው

አበው እንደሚሉት ቆማጣን ቆማጣ ብለው ካላሉት
ደስ ይለዋል አሉ ገብቶ መፈትፈት

እሰከ ዛሪ ድረስ ትግል ብለን ያልነው
ለማንም አልበጀ ጊዚ ማባከን ነው

ፈረሱን ከጋሪው ማስቀደም አለብን
የተገላቢጦሽ የትም አያደርሰን

እኒ እንደሚመስለኝ መድሀኒት የምለው
የትግል ታክቲኩን ቶሎ መቀየር ነው

ባዶውን ከቀረው ካገልጋዩ ጋሪ ከምንታገል
ሳንውል ሳናድር ትግሉን ወደ ጊታው ማዞር ይገባናል

ግፈኛውን ፈረንጅ እኛ ስናቀው
ዛሩ ደንገጥ ብሎ የሚያዳምጠው
ስታከብረው ሳይሆን ስትገርፈው ነው

የትም ይሁን የት ተዝናንቶ መኖር ነው የሱ ፍላጎት
ምንም ደንታ የለው እኛ ብንሰደድ ወይም ብንሞት

ሰለዚህ ወገኒ ዶክተር ፕሮፌሰር ምሁራኑ ሁሉ
ታክቲክህን ቀይር እስከመጨረሻው እንዲሰምር ትግሉ

መልፈስፈስ እናቁም እንሁን ኮስታራ
ባንዲራው ይሰቀል በቋራ ተራራ

እንቢልታው ይነፋ ከበሮው ይደለቅ
የታጋዮች መንደር ይበል ደመቅ ደመቅ

ከተማ ቁጭ ብለን በራብ ከሚፈጀን
ወይም እንደ ፍየል ጢማችንን ይዞ ከሚጎትተን
እንጠቀምበት ጋራ ሸንተረሩን እንዳባቶቻችን
በኩራት እንድትኖር እስከ ዘላለሙ ኢትዮጵያ አገራችን!!!

---

24-07-2012